# POLICY BOARD OF EDUCATION OF MONTGOMERY COUNTY

ተዛማጅ ግብአቶች፡- ABA, ACF, COA-RA, COG-RA, DJA-RB, EGB-RA, EGF-RA, IGT-RA, IIB, IIB-RA, ITA-RA, JHC, JHC-RA, JHF, JHF-RA, JOA-RA, KBA, KGA-RB

ኃላፊነት ያላቸው ጽ/ቤቶች፡- Office of Teaching, Learning, and Schools Office of Engagement, Innovation, and Operations/የማስተማር መማር እና ትምህርት ቤቶች ጽ/ቤት የስምሪት፣ ኢኖቬሽን፣ እና የስራ ሒደት ጽ/ቤት

## ትምህርታዊ ቴክኖሎጂ/Educational Technology

A. **ዓላማ**

1. የማስተማር እና የመማር ጥረትን ለመደገፍ እንዲሁም የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ዋና ዋና ሥራዎችን ለማከናወን ውጤታማ፣ ትክክለኛ፣ እና ስትራቴጂያዊ የቴክኖሎጂ ሪሶርሶችን የማቀናጀት መመሪያ ማዘጋጀት።
2. የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ መማር እና ማስተማርን ለመደገፍ ለግንኙነት፣ ለትብብር፣ ለፈጠራ፣ እና ለግኝት ደህንነቱ በተጠበቀና ሀላፊነት በተሞላበት ሁኔታ ቴክኖሎጂን በመጠቀም ለሁሉም ተማሪዎች እና ሠራተኞች ሚዛናዊ/ፍትኃዊ የትምህርት ተደራሽነት እንዲኖር ያለውን ቁርጠኝነት እንደገና ማረጋገጥ።

B. **ፍሬ ነገሮች (ISSUES)**

ቦርዱ የማስተማር እና የመማር ጥረት እንዲሁም የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስን (MCPS) ዋና ዋና፣ መሠረታዊ አሠራር-ተግባርን ለመደገፍ የቴክኖሎጂ ሪሶርሶችን ጥምረት ለመምራት የሚከተሉትን መርሆዎች ያረጋግጣል፡- ቴክኖሎጂ የሥርዓተትምህርት ግቦችን የሚደግፍ የማስተማር እና የመማር ሂደት አንድ አካል ነው፤ ሠራተኞች እና ተማሪዎች የቴክኖሎጂ መገልገያዎችን በብቃት፣ በንቃት፣ እና ኃላፊነት በተሞላበት ሁኔታ ይጠቀማሉ፤ ቴክኖሎጂ ተማሪዎች በርካታ የተለያዩ የትምህርት ፍላጎቶቻቸውን እንዲያሳኩ ይረዳቸዋል፤ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ትምህርት እና የስራ ሒደትን ለመደገፍ በአጠቃላይ ተግባራዊ የቴክኖሎጂ መሠረተ ልማት ያቀርባል፤ እና የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የበለጸገ እውቀት ለማግኘት ትምህርታዊ ቴክኖሎጂ መጠቀምን፣ ዲጅታል ይዘት እንዲኖራቸው፣ እና ሁሉም ተማሪዎች በርካታ-ልዩ ልዩ የመማር ፍላጎታቸውን ለማሣካት የቦርዱን ራዕይ ቅርጽ ለማስያዝ፣ ለማዳበር፣ እና ለማፋጠን ከበርካታ ባለድርሻ አካላት ጋር ይሠራል።

C. **አቋም**

1. ቴክኖሎጂ የሥርዓተ ትምህርት ግቦችን የሚደግፍ የማስተማር እና የመማር ሒደት አካል ነው።
   a) በአገር አቀፍ እና በስቴት ደረጃ የሚገኙ የትምህርት ኤጀንሲዎች ተማሪዎች፣ ትምህርት የሚሰጡ ባለሙያዎች፣ እና የትምህርት አመራሮች ቴክኖሎጂን እና ዲጅታል የመማሪያ መሣሪያዎችን ስለሚጠቀሙበት መስፈርት የሚያስረዱ መመሪያዎች አሉ። እንደነዚህ ያሉ መስፈርቶች በትምህርት ቤት ዲስትሪክቶች፣ በሜሪላንድ እና በጠቅላላው ዩናይትድ ስቴትስ አካደሚያዊ ምጡቅነትን ለማዳበር/ለማስፋፋት የቴክኖሎጂ አጠቃላይ ውህደትን ይመራሉ።

b) አግባብነት ያለው ትምህርታዊ ቴክኖሎጂ አጠቃቀምን በማስፈን የትምህርት ግቦችን ለማበልጸግ፣ ተገቢው የዲጅታል መሣሪያ በፍትኃዊነት/በሚዛናዊነት ተደራሽ መሆኑን ለማረጋገጥ፣ ስለቴክኖሎጂ እና መረጃ/ኢንፎርሜሽን አጠቃቀምን በሚመለከት ኃላፊነት የተሞላበት ማህበራዊ ግንኙነትን ለማዳበር፣ የሜሪላንድ ዲጅታል የትምህርት መስፈርቶች ለዲጂታል መረጃ እና ለትምህርት ቴክኖሎጂ ደህንነቱ የተጠበቀ፣ ህጋዊ እና ስነምግባርን የጠበቀ በፖሊሲዎች ውስጥ የሚነሱ ቁልፍ ጉዳዮችን ለይቷል።

c) የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በቦርድ ድንጋጌ መሠረት ከአግባብነት እና ሚዛናዊነት መርህ ጋር በማጣጣም ቴክኖሎጂን ከማስተማር እና የስራ ሒደት ጋር ያቀናጃል –

1) የቦርድ ፖሊሲ ACA - "Board Policy ACA" ፀረመድሎአዊነት፣ ፍትሕ፣ እና ባህላዊ ብቃት/Nondiscrimination, Equity, and Cultural Proficiency፣

2) የአካል ስንክልና ያላቸው አሜሪካኖችን የሚመለከት ደንብ/Americans with Disabilities Act፣ እና የስቴት ህጎች እና ደምቦች በሚደነግጉት መሠረት ስለ ተደራሽነት የስቴት እና የፌደራል መስፈርቶች፣ እና

3) ስለ ትምህርት ዩንቨርሳል ዲዛይን የተደራሽነት መስፈርቶች

d) ስለተማሪ መማር ከሜሪላንድ መስፈርቶች እና ከቦርድ ፖሊሲዎች እና ግቦች ጋር በማጣጣም፣ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ለትምህርት ስኬታማ የሆነ የትምህርታዊ ቴክኖሎጂ አጠቃቀም በማስረጃ ላይ የተሞረኮዙ ስትራቴጂዎች እና ዘዴዎች ላይ እምነት ይጥላል። የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የትምህርታዊ ቴክኖሎጂ ሪሶርሶችን ከሚያስፈልጉ የትምህርት ውጤቶች ጋር ይቆጣጠራል እና ያቀናጃል። በማስረጃ ላይ የተሞረኮዙ የማስተማር ምርጥ ተሞክሮዎችም መመሪያ ይሆናሉ–

1) የትምህርታዊ ቴክኖሎጂ ምርቶችን ማዳበር እና/ወይም መምረጥ፣ መለየት፣ ግዢ እና

2) በቀጥታ ማስተማር፣ የተቀናጀ ትምህርት፣ እና የርቀት ትምህርትን የሚያካትት በተለያዩ የትምህርት አቅጣጫዎች፣ ማስተማርን እና መማርን ለመደገፍ እና ለማዳበር የታለመ ግብ ያለው/አላማ ያለው እና ስትራቴጂያዊ የሆነ የሪሶርሶች ጥምረት።

e) ተማሪዎች እና ሠራተኞች የስቴት መስፈርትን የጠበቀ የቴክኖሎጂ መሠረታዊ እውቀት (ሊተረሲ) እንዲያገኙ ቦርዱ ያለውን ድጋፍ ያረጋግጣል። በዚህ ፖሊሲ አላማ መሠረት፣ የቴክኖሎጂ ትምህርት (ሊተረሲ) ማለት ራስን ችሎ ለብቻ መሥራት ለመቻል እና በቴክኖሎጂ በሚሠራበት አካባቢ ከሌሎች ጋር ለመስራት፣ እና ኃላፊነት የተሞላበት፣ በተገቢ ሁኔታ እና ስኬታማ የሆነ የቴክኖሎጂ መሣሪያዎች አጠቃቀምን ተደራሽነት፣ መምራት፣ ማቀናበር፣ ግምገማ፣ መረጃን መፍጠር እና ኮሙኒኬት ማድረግ ነው። በተጨማሪ፣ የቦርዱ ፍላጎት ተማሪዎቻችን እና ሠራተኞቻችን በእውቀት ውሳኔ ሰጪነት እና የእውቀት ፈጣሪዎች በመሆን፣ እና ችግሮችን ለመፍታት ስለሚጠቀሙበት ቴክኖሎጂ እውቀት እንዲኖራቸው እና ሃሳብን በማስተካከል ቴክኖሎጂን መጠቀም እንዲችሉ ነው።

f) ከስቴት መስፈርቶች/መመዘኛዎች ጋር በተጣጣመ መልኩ ተማሪዎች እና ሠራተኞች የኢንፎርሜሽን እውቀት እንዲኖራቸው ለመደገፍ ቦርዱ ያለውን ዝንባሌ ያረጋግጣል። የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ጥያቄን/ምርመራን በማበረታታት እና የሚማሩትን መረጃን በማግኘት ትክክለኝነቱን እንዲያረጋግጡ፣ የተለያዩ መሣሪያዎችን በመጠቀም ከዲጅታል ምንጮች መረጃ ለመውሰድ በጥንቃቄ እንዲያስቡ፣ እና የትምህርት ግቦችን

ስኬታማነት ከፍ ለማድረግ በሚድያ-የበለጸጉ ሪሶርሶችን በማሟላት ክህሎትን ያስታጥቃል።

2. ሠራተኞች እና ተማሪዎች የቴክኖሎጂ አቅርቦቶችን በብቃት፣ ዓላማ ተኮር፣ እና ኃላፊነት በተሞላበት አካኋን እንደሚጠቀሙባቸው ቦርዱ ይጠብቃል።

a) የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ከማስተማር ሙያ ጋር የትምህርት መርጃ ቁሳቁሶችን ተደራሽነት ስለማቀናጀት የስቴት እና የፌዴራል መስፈርቶች በሚደነግጉት መሠረት ሠራተኞች ቴክኖሎጂን ከማስተማር ሥራ ጋር በብቃት ማቀናጀት እንዲችሉ ተፈላጊውን የተወዳዳሪነት ብቃት፣ ችሎታ፣ አቅም በመለየት ተገቢውን የሙያ ትምህርት እና የድጋፍ ስትራቴጂዎችን ይሰጣል። የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሠራተኞች የሙያ ለማጀች (ተማሪዎች) ድጋፍ እና ትምህርት በሚሰጣቸው ወቅት ትምህርታዊ ቴክኖሎጂን እንዲጠቀሙ ይፈቅድላቸዋል።

b) የማስተማር ተሞክሮዎች ትምህርትን በንቃት፣ በድርጊት/አሳታፊ፣ ትርጉም ያለው፣ እና ማህበራዊ የእርስበርስ አገናኝ ለማድረግ በተለያየ አይነት የማስተማር ዘዴዎች እና ስልቶች የትምህርታዊ ቴክኖሎጂን አጠቃቀም በአግባቡ ሚዛናዊ ያደርጉታል። ይህንንም በማድረግ፣ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የተማሪዎችን እድሜ እና የእድገት ደረጃ ግምት ዉስጥ ያስገባል እናም ከዲጅታል ይዘት ጋር የሚያጠፉትን ያህል ጊዜ መቆጣጠር አስፈላጊ መሆኑን የሚገነዘብ ሲሆን የተለያየ አይነት የመማሪያ ስልቶችን እና ዘዴዎችንም ያቀርባል።

c) ዲጅታል ዜጋ እና ኃላፊነት የተሞላበት አጠቃቀም

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ጤናማ፣ ህጋዊ እና ስነምግባራዊ የዲጅታል መረጃ አጠቃቀምን እና የቴክኖሎጂ ናሙናዎችን ያዳብራል እና የአፈጻጸም መመሪያ ይመሠርታል። እናም እንደዚህ አይነት መረጃ/ኢንፎርሜሽን አግባብነት በሌለው ሁኔታ መጠቀምን ለመከላከል፣ መፍትሔ ለመስጠት ተገቢውን እርምጃ ይወስዳል። ተማሪዎች እና ሠራተኞች መብቶችን፣ ኃላፊነቶችን፣ እና የመኖር፣ የመማር፣ እና የመሥራት እድሎችን እርስ በርስ በተገናኘ የዲጅታል ዓለም፣ ጤናማ፣ ህጋዊ፣ እና ስነምግባር የተሞላበት አጠቃቀምን ቦርዱ የማስገንዘብ ፍላጎት አለው። ተማሪዎች ማድረግ ያለባቸው –

1) የዲጅታል መገናኛዎቻቸውን ማንነት እና ዝና ማጣራት እና መምራት እንዲሁም ስለ ግል መረጃ መፍጠር፣ መቀበል/መውሰድ/ማግኘት፣ እና ማሠራጨት የሚኖረውን የአጭር-እና የረዥም ጊዜ እንደምታዎችን ግንዛቤ መጨበጥ።

2) ቴክኖሎጂን ሲጠቀሙ ማህበራዊ ግንኙነቶችን በሚመለከት አዎንታዊ፣ ቅንነት የተሞላበት፣ ጤናማ፣ ህጋዊ እና መልካም ስነምግባርን የተላበሰ ባህርይ እንዲኖራቸው፣

3) የሌሎችን አእምሯዊ የፈጠራ ውጤት ሲጠቀሙ የባለቤትነትን መብቶች የማወቅ ግዴታ እና የሌሎችን መብት የማክበር ግንዛቤ እንዲላቸው ማረጋገጥ፣ እና

ዲጂታል ብትህውነትን/ግላዊነትን እና ደህንነትን ለማስጠበቅ የግል መረጃቸውን ማኔጅ ማድረግ፣ በይነመረብ ላይ የሚያደርጉትን ዳሰሳ ለመከታተል የሚችሉ የመረጃ አሰባሰብ ቴክኖሎጂዎች መኖራቸውን ማስገንዘብ።

d) የመረጃ-ዳታ ብትህውነት እና የመረጃ-ዳታ ደህንነት

በቦርድ ፖሊሲ-Board Policy KBA፣ ድንጋጌ መሠረት፡- የተማሪዎች እና የሠራተኞች መረጃ

ግላዊነት እና ደህንነት በትክክል የሚጠበቅ ስለመሆኑ ቦርዱ ያለውን ቁርጠኝነት ያረጋግጣል ህዝባዊ መረጃ-Public Information፣ እና ስለ ዳታ መሰብሰብ፣ ግላዊነት፣ እና ደህንነት ከሁሉም የስቴት እና የፌደራል ህጎች ጋር የማይጣረስ መሆኑን ቦርዱ ያረጋግጣል።

1) እነዚህ መረጃዎች ለማስተማሪያ እና ለመማሪያ እንዲሁም ለትምህርት ቤት የሥራ ሂደት በከፍተኛ ደረጃ ጥቅም እየሰጡ ሳለ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) መረጃን-ኢንፎርሜሽንን እና የኢንፎርሜሽን ሲስተሞችን ባልተፈቀደላቸው ሰዎች ተደራሽነት፣ አጠቃቀም፣ መታየት/መገለጥ፣ መደናቀፍ፣ መለወጥ-ማሻሻል፣ ወይም ማቋረጥ እንዳይኖር ለመከላከል ተገቢ የሆኑ ሪሶርሶችን ይመድባል።

2) የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ስለ ተማሪ እና የሠራተኛ ዳታ ግላዊነትን ለመጠበቅ-ለመከላከል የተለየ የአሠራር ሲስተሞችን፣ ፕሮቶኮሎችን፣ እና መመሪያዎችን ያዘጋጃል።

3) ሊታይ/ሊታወቅ የሚችል የግላዊ መረጃ-ኢንፎርሜሽን እና ሌላ ጥንቃቄ ስለ ሚያሻው መረጃ አጠቃቀም እና አያያዝን በተመለከተ ሠራተኞች ቀጣይነት ባለው የሙያ ማዳበር ትምህርት ላይ ይሳተፋሉ።

4) የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ከተማሪዎች ጋር የማስተማሪያ ቴክኖሎጂዎችን ለመጠቀም ሲመርጥ የዳታ/መረጃ ግላዊነት እና ደህንነት በእውቀት መወሰንን ያካትታል።

3. ቴክኖሎጂ የተማሪዎችን ልዩ ልዩ የመማር ፍላጎቶች በማሟላት እና ሌሎች በርካታ ፍላጎቶችንም ለማከናወን ይረዳል-ያግዛል።

a) እየተፈጠሩ ያሉት ቴክኖሎጂዎች መደበኛ/የተለመደ ማስተማርን በተጨማሪ ድጋፍ-እገዛ እንዲሁም በተፋጠነ እና የዳበረ የማስተማር ሒደት ፈርጀ- ብዙ ጣልቃገብነቶችን እድል ይሰጣል።

b) የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በመማሪያ ክፍል ውስጥም ሆነ ውጭ የተማሪዎችን ፈለግ ለመርዳት፣ በዚህ ብቻ ሳይወሰን የርቀት ወይም ጣምራ ትምህርቶችን ጨምሮ የተማሪዎችን የተለያዩ ፍላጎቶች ለማሳካት አግባብነት ያላቸው የትምህርት መርጃ ቴክኖሎጂዎችን ያሥሣል፣ ያዳብራል፣ እና/ወይም ይመርጣል።

c) የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የተማሪ ትምህርትን እና የተማሪ ስኬታማነት ዓላማን የሚያረጋግጡ ማስረጃዎችን በመቆጣጠር ረገድ በርካታ-እርምጃዎችን ይተገብራል። ቀጣይነት ያለው የተማሪ ግስጋሴን መቆጣጠር ተማሪዎች ወቅታዊ እና ተገቢውን ድጋፍ ማግኘታቸውን፣ ትኩረት ያለው ጣልቃገብነትን፣ የተፋጠነ፣ እና የዳበረ ድጋፍ ማግኘታቸውን ያረጋግጣል። የተለየ ትኩረት ስለሚሰጣቸው የተማሪዎች ቡድኖች አሠራር በልዩ መስፈርት/መለኪያ የተጠቃለለ ሪፖርት ስለ ሚዛናዊነት ተጠያቂነት፣ እና በተደራሽነት ዳታ ላይ የተመሠረተ ትንታኔ፣ እድል፣ እና የሁሉንም ተማሪዎች ስኬታማነት ያረጋግጣል።

d) የማስተማሪያ መጽሐፍት፣ ዲጂታል መሣሪያዎች፣ እና የህትመት ዲጅታል ሪሶርሶች መጠነ ሰፊ ስለሆነ እንደልዩነታቸዉ መጠን በየግል ለመጠቀም እንዲችሉ እየተመረጡ በመገዛት ይሠራጫሉ።

e) የማስተማርን ሒደት ለመደገፍ ስትራቴጂያዊ የሆነ የዲጅታል መሣሪያዎች ቅንጅት ለተማሪዎች ለቴክኖሎጂ ሚዛናዊ የሆነ ተደራሽነትን ትኩረት የሚሰጥ እና ከትምህርት ቤት ውጪ ትምህርታዊ

ቴክኖሎጂን ለመጠቀም ተማሪዎች የሚያጋጥማቸውን በአይነቱ ልዩ የሆነ ተግዳሮቶችን ያገናዘበ ነው። የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ለእነዚህ የሚዛናዊነት እንደምታዎች፣ እንደአግባብነቱ፣ የተለያዩ አይነት የትምህርት ስልቶችን ይጠቀማል፣ የትክክለኛ ማገናኘት ጉዳይ ስጋት ብቻም ሣይሆን ተማሪዎች ከትምህርት ቤት አካባቢ ውጪ እንደዚህ አይነት ትምህርታዊ ቴክኖሎጂ ሲያስፈልጋቸው ጭምር ጥንቃቄ የተሞላበት ትኩረት ይሰጣል።

4. የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የማስተማርና የሥራ ሒደትን ለማቀላጠፍ፣ እና ከማህበረሰብ ጋር ለመገናኘት የሚያስችል ሰፊ/አጠቃላይ እና ዓላማውን በግልጽ የሚያሳይ ቴክኖሎጂ መሠረተ ልማትን/infrastructure ይዘረጋል።

   a) ለ MCPS የማስተማር ፕሮግራሞች እና የሥራ እንቅስቃሴዎች ከፍተኛ ጥራት ያለው አገልግሎት የሚሰጥ ጥሩ ውጤት ያለው፣ ፍቱን፣ ተገቢ የሆነ፣ አስተማማኝ፣ እና በተመጣጠነ ወጪ ቴክኖሎጂን ለማግኘት እና ሥራ ላይ ለማዋል የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ዘዴ የተሞላበት-ሥርዓት ያለው አቀራረብ እንደሚኖረው ቦርዱ ያምናል።

   b) ቴክኖሎጂ የማስተማር-መማር እና የሥራ ፍላጎቶችን የማሟላት ችሎታ ከጊዜ ወደ ጊዜ በፍጥነት ይለወጣል። ዳሩ ግን፣ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ወቅታዊና አዲስ እየወጣ ያለ ቴክኖሎጂን ስለ ቴክኖሎጂው፣ የመሠረተልማት ፍላጎት ካለው ሪሶርስ ጋር በማመዛዘንና በጥንቃቄ በማጥናት የተሻለና ከፍተኛ ጠቀሜታ ለማግኘት እና ጊዜው ያለፈበትን ቴክኖሎጂ በአዳዲስ ቴክኖሎጂ ለመተካት ቁርጠኝነት አለው።

   c) የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በትምህርት ክፍሎች መካከል ግንኙነትና ትብብርን ለማዳበር፣ ከትምህርት ቤት ውጭ የትምህርት እድሎችን ለማስፋፋት፣ እና በተማሪዎች፣ አስተማሪዎች፣ ሠራተኞች፣ ወላጆች/ሞግዚቶች፣ እና በማህበረሰብ አጋሮችን መካከል የመረዳዳት ግንኙነትን መንፈስ ለማበልፀግና ለማስተባበር የቴክኖሎጂ አቅምን በማደርጀት ይጠቀማል።

      1) የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሁሉም የመማሪያ ክፍሎች፣ የሚድያ ማዕከላት፣ እና ጽ/ቤቶች-ቢሮዎች በተገቢ መሠረተልማት መገናኘታቸውንና ተገቢ የቴክኖሎጂ መገልገያዎች እንዳሏቸውና ለማስተማር፣ ለመማር፣ ለማኔጅመንት፣ እና ለእለት-ተ-እለት የሥራ ክንውን ሚዛናዊ የሆነ በቀላሉ የቴክኖሎጂ መገልገያዎችን ተደራሽነት ማግኘታቸውን ለማረጋገጥ መሠረታዊ የሆኑ መስፈርቶችን ያዘጋጃል።

      2) የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በእነዚህ ሲስተሞች እና አውታረመረቦች/systems and networks የሚተላለፉ ሪኮርዶችን እውቅና በመስጠትና ደህንነታቸውን በማረጋገጥ ለሲስተሞቹና ለአውታረመረቦች ሰፊ ተደራሽነትን ይሰጣል። ተግባራዊ የሚደረጉ ህጎችን በሙሉ በማክበር ደህንነታቸውን ለማስጠበቅ የመከላከያ ዘዴዎች ይኖራሉ።

   d) የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ለተማሪዎች፣ ለመምህራን፣ እና ለሌሎች የሥራ ባልደረቦች ቨርቹወል ትምህርት ላይ ሙሉ በሙሉ ለመሣማራት ሁኔታዎች በሚፈቅዱለት መጠን የሚያስፈልጋቸውን ቴክኖሎጂ እና ድጋፍ ለመስጠት ቁርጠኛ ነው።

5. በትምህርታዊ ቴክኖሎጂ፣ እና በዲጅታል ይዘት በመጠቀም ለመማር እንዲያስችላቸው፣ የሁሉንም ተማሪዎች የተለያዩ ፍላጎቶችን ለማሟላት ቦርዱ ያለውን ራዕይ ለመተግበር፣ ቅርጽ ለማስያዝ፣ ለማዳበር፣ እና ለማፋጠን የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ከበርካታ ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር-ትኩረት ይሰጣል።

a) ስለ ትምህርታዊ ቴክኖሎጂ እቅድ የማዘጋጀት ኃላፊነት ያለባቸው የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ክፍሎች/ዩኒቶች ውጤታማ የሆኑ እና የተመጣጠነ ወጪ ያላቸውን አፕሊኬሽኖች ለመለየት እርስበርሳቸው፣ እንዲሁም ከካውንቲው፣ ስቴት፣ እና የመንግሥት ኤጀንሲዎች ጋር የወቅቱን፣ የተሻሻሉ፣ እና አዲስ የሚወጡትን የንግድ ቴክኖሎጂዎችን ለመመርመር እና ለይቶ ለማወቅ፣ ወይም አስፈላጊ ከሆነ ለማሻሻል፣ በትብብር ይሠራሉ።

b) የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ትምህርታዊ ቴክኖሎጂን በአግባቡ ለተማሪዎች ተደራሽነት እንዲኖራቸው እና እነዚህን ቴክኖሎጂዎች በትምህርት ቤት ክልል እና ከዚያ ባሻገር ለመጠቀም እንዲያስችላቸው ድጋፍ ለመስጠት ከወላጆች/ሞግዚቶች ጋር እና ከማህበረሰብ ቡድኖች ጋር አጋርነትን ይገነባል-ይጠብቃል።

D. **ተፈላጊ ውጤቶች**

1. የትምህርት መርጃ ቴክኖሎጂ በአግባቡ፣ በስኬታማነት፣ በዘላቂነት፣ እና በሚዛናዊነት ከሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የትምህርት አሰጣጥ እና የሥራ ሒደት ጋር በማጣመር የተማሪዎችን ጥረት እና ክንውን፣ የሠራተኞችን የእለት ተእለት ስራ ውጤታማነት፣ እና ብቃት ጋር የተጣመረ ይሆናል።
2. አዲስ የሚወጣ ትምህርታዊ ቴክኖሎጂን ማዳበር እና/ወይም መምረጥ የቴክኖሎጂ ኢንቨስትመንቶች በሚዛናዊነት፣ ተደራሽነት፣ እና ትምህርታዊ ቴክኖሎጂ በአግባቡ ወደ ፔዳጎጂካል ትግበራ መቀናጀቱ በሚያስከትለው ውጤት/implications ላይ ትኩረት ይሰጣል።
3. ሁሉም ትምህርት ቤቶች እና ጽ/ቤቶች-ቢሮዎች ሚዛናዊ እና አግባብነት ያለው መሠረተ ልማት/infrastructure እና የግንኙነት ብቃት፣ ያሉት ሪሶርሶች በሚፈቅዱት መጠን እንዲኖራቸዉ ይደረጋል፣ እና የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ስለነዚህ መሠረተልማቶች/infrastructure እና ግንኙነቶች ብቃት መደበኛ ዳሰሳ ይደረጋል።

E. **ግምገማ እና ሪፖርት**

1. የዚህን ፖሊሲ አፈጻጸም የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት ይቆጣጠራል፣ ይገመግማል፣ እና በየወቅቱ ለቦርድ ሪፖርት ያቀርባል።

2. ይህ ፖሊሲ በትምህርት ቦርድ የፖሊሲ ግምገማ ስርዓት መሠረት ይሻሻላል።

**ተዛማጅ ምንጮች:** *Family Educational Rights and Privacy Act*, 20 U.S.C §1232g; Protection of Pupil Rights Amendment (PPRA), 20 U.S.C. §1232h, 34 CFR Part 98, (2000 and Supp IV 2004); Section 504 of the Rehabilitation Act of 1973, as amended, 29 U.S.C. Sec 794; *Americans with Disabilities Act* (ADA), 42 U.S.C. 12131 et seq; *Children's Internet Protection Act* (CIPA), 47 U.S.C. §254(h)(5)(B)-(C), 254(l); *Children's Online Privacy Protection Act of 1998 (COPPA), 15 U.S.C.6501-6505*, 16 CFR Part 312; *Public Information Act of Maryland*, Ann Code of Maryland, General Provisions Article §§4-101 through 4-601; *Maryland Student Data Privacy Act of 2015,* Ann Code of Maryland, Education Article, §4-131 and 7-443; Code of Maryland Regulations §13A.03.02.03.B(8) and §13A.06.05.02-.04, .06; *Maryland Digital Learning Standards,* Maryland State Department of Education (MSDE), May 2019; *Technology Education Standards: Grades 6-12*, MSDE, January 2016; *Health and Safety Best Practice Guidelines: Digital Devices*, MSDE, July, 2019; International Society for Technology in Education Standards Administrators, Education Leaders, Educators, and Students

***የፖሊሲው ታሪክ፦*** ዲሴምበር December 8/ 1993 በውሳኔ ቁጥር- No 863-93 በሥራ ላይ ከዋለ በኋላ ፌብሯሪ 9/2020 ተሻሽሏል።

***ማስታወሻ፦*** ከውሳኔ ቁጥር/Resolution No 863-93 በፊት፣ ይህ ርእስ እንደሚከተለው ይመራ ነበር፦ ኮምፒውተሮችን ለማስተማሪያነት መጠቀም/Instructional Use of Computers፣ በሥራ ላይ የዋለው በውሳኔ ቁጥር Resolution No 995-83፣ ዲሴምበር 13/1983 ነው፣ በውሳኔ ቁጥር/Resolution No 333-86 መሠረት ጁን 12/1986፣ እና በውሳኔ ቁጥር/Resolution No 458-86፣ ኦገስት 12/1986 የተሻሻለ ሲሆን፣ በውሳኔ ቁጥር/Resolution No 863-93፣ ዲሴምበር 8/1993 ተሽሯል።